ምክንያተ ፡ ጽሒፎቱስ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ኀበ ፡ ሰብአ ፊልጵስዩስ ፡ ኮነ ፡ በእንተ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ዘበእንቲአሆሙ ፡ አዘዘ ፡ ዝንቱ ፡ ሐዋርያ በመልእክቱ ፡ ከመ ፡ ኢይትወከፍዎሙ ፡ ምእመናን ፡ ወኢይስምዑ ፡ ቃሎሙ ፡ ወበእንተዝ ፡ መምህራን ፡ እለ ፡ ተንሥኡ ፡ በፈቃዶሙ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ እነ ፡ አጠምቅ ፡ ወአነ ፡ እክውን ፡ መምህረ ።

ወዘንተ ፡ ይገብሩ ፡ ለኀሢሠ ፡ ረብሕ ፡ ዓለማዊ ወፊልጵስዩስኒ ፡ ሊቅተ ፡ መቄዶንያ ፡ ይእቲ ።

ወሰብእ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡ እሙን ፡ ቀዳሚ ፡ በስብከቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ሐዋርያ ።

ወሶበ ፡ ሖረ ፡ እምኔሆሙ ፡ ኀደጎ ፡ ለአፍሮዲጡ ፡ ረድኡ ፡ ከመ ፡ ይገሥጾሙ ፡ ኢያምጽኡ ፡ ካልአ ፡ ትምህርተ ።

ወዐበዩ ፡ ትእዛዞ ፡ ለአፍሮዲጡ ፡ ወተንሥኡ ፡ በፈቃዶሙ ፡ ላዕለ ፡ መዓርግ ፡ ዐቢይ ፡ ወመሀሩ ።

በከመ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ ሐዋርያ ፡ ወአለሰ ፡ በትዝኅርቶሙ ፡ ወበተቃሕዎቶሙ ፡ ይነግሩ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ አኮ ፡ በንጽሕ ፡ ዳዕሙ ፡ ይትሔዘቡ ፡ ከመ ፡ ገቢሮሙ ፡ ኪያሁ ፡ ይወስኩ ፡ ሊተ ፡ ሕማመ በመዋቅሕትየ ።

ወዓዲ ፡ አዘከሮሙ ፡ ከመ ፡ ይትመሀሩ ፡ ተግሣጸ ፡ ወትሕትና ፡ እምኀበ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሐልዩ ፡ ለነኒ ፡ ዘከመ ፡ ገብረ ፡ ለነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ዘውእቱ ፡ እርአያሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አኮ ፡ ሐይዶ ፡ ዘኮነ ፡ እግዚአብሔር ፡ እላ ፡ አትሐቶ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ገብር ።

ወአለሰ ፡ በቅንዓቶሙ ፡ ይነግሩ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ሐዋርያተ ፡ ሐሰት ፡ ዘበእንቲአሆሙ ፡ ጸሐፈ ከመ ፡ ይትዐቀቡ ፡ ሕዝብ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ዑቅዎሙ ፡ ለከለባት ፡ ወዑቅዎሙ ፡ ለምቀራን ፡ በግዝረት ።

እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ኮኑ ፡ ቀናዕያነ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ሐዋርያ ፡ በእንተ ፡ ክልኤቱ ፡ ምክንያት ።

፩ሰ ፡ በእንተ ፡ ትምህርተ ፡ ኦሪት ፡ ዘተገድፈት ፡ በትምህርቱ ፡ ወካልኡኒ ፡ በእንተ ፡ እምኃ ፡ ዘፈነዉ ፡ ሰብአ ፡ ፊልጵስዩስ ኀበ ፡ ጳውሎስ ፡ በእደ ፡ አፍሮዲጡ ።

ወጸሐፈ ፡ ዘንተ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ሙቁሐ ፡ በሮሜ ፡ አመ ፡ ሙቃሔሁ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወፈነዎ ፡ በእደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ወአፍሮዲጡ ።

ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ለፊልጵስዮስ ፡ ሰዎች ክታብ ፡ የጻፈበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ሐዋርያ ፡ በዚሁ በክታቡ ፡ ምእመናን ፡ ቃላቸውን ፡ እንዳይሰሟቸው ትምህርታቸውን ፡ እንዳይቀበሏቸው ፡ ስለጻፈባቸው ስለቢጽ ፡ ሐሳውያንና ፡ በፈቃዳቸው ፡ እኔ ፡ አጠምቃለሁ ፡ እኔ ፡ አስተምራለሁ ፡ እያሉ ፡ ስለተነሡ መምህራን ፡ ነው ።

ይህንም ፡ ሥጋዊ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ሽተው ይሠሩታል ፡ ፊልጵስዩስም ፡ የመቄዶንያ ፡ መዲና ፡ ናት ።

በውስጧ ፡ የሚኖሩትም ፡ ሰዎች ፡ መጀመሪያ በርሱው ፡ ስብከት ፡ አምነዋል ።

ከነሱም ፡ በሔደ ፡ ጊዜ ፡ ካስተማራቸው ፡ ትምህርት ፡ ወጥተው ፡ ሌላ ፡ ትምርት ፡ እንዳያመጡ ፡ ይመክራቸው ፡ ያስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ አፍሮዲጡን ፡ ትቶት ፡ ሔደ ።

ለአፍሮዲጡ ፡ እንታዘዝም ፡ ብለው ፡ በፈቃዳቸው ፡ ከደገኛው ፡ ማዓርግ ፡ ደርሰው ፡ ያስተምሩ ፡ ጀመር ።

ማን ፡ ከማን ፡ አንሶ ፡ ብለው ፡ በትዕቢት ፡ በጸብ ፡ በክርክር ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ አናስተምራለን ፡ የሚሉ ፡ እኒህ ፡ ይህን ፡ አድርገው ፡ በዕስራቴ ፡ ላይ ፡ ብስጭት ፡ ሊጨምሩልኝ ፡ ሽተው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእውነት ፡ የሚያስተምሩ ፡ ንጹሓን አይደሉም ፡ ብሎ ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ እንደተናገረ ።

ዳግመኛም ፡ ተግሣጽን ፡ ትሕትናን ፡ ከክርስቶስ ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ለኛ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ትሕትና ፡ እንዳደረገልን ፡ አስቡ ፡ እያለ ፡ አሳስቧቸዋል ።

ክርስቶስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመልክ ፡ የሚመስለው ፡ በባሕርይ ፡ የሚተካከለው ፡ ሲኾን ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ እርአያ ፡ ገብር ፡ ነሣ ፡ እንጂ ፡ ቀምቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ የኾነ ፡ አይደለም ፡ እያለ ፡ አሳሰባቸው ።

ይንደዱው ፡ ይቈጧው ብለው ፡ የሚያስተምሩም ፡ ሕዝቡ ፡ ከነሱ ፡ ይጠበቁ ፡ ዘንድ ፡ በኒያ ፡ ለከፍካፎች ፡ በኒያ ፡ ግዘራን ፡ ነን ፡ ባዮች ፡ ዕወቁባቸው ፡ ብሎ ፡ ይህ ፡ ሐዋርያ ፡ ስለነሱ ፡ የጻፈባቸው ሐሰተኞች ፡ መምህራን ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ናቸው

እነሱ ፡ ስለኹለት ፡ ነገሮች ፡ በቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይቀኑበት ፡ ስለነበረ ።

ከኹለቱም ፡ አንዱ ፡ ኦሪት ፡ በርሱ ፡ ስብከት ስለወደቀች ፡ ነበረ ። ኹለተኛውም ፡ የፊልጵስዩስ ፡ ሰዎች ፡ በአፍሮዲጡ ፡ እጅ ፡ ለቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ስለላኩ ፡ ነበረ ።

ይህን ፡ ክታብ ፡ በመጀመሪያ ፡ እስራቱ ፡ በሮሜ ፡ ታስሮ ፡ ሳለ ፡ ጽፎ ፡ በጢሞቴዎስና ፡ በአፍሮዲጡ ፡ እጅ ፡ ላከው ።

www.ethiopianorthodox.org

ፊልጵስዮስ ፡ በመቄዶንያ ፡ ያለች ፡ መዲና ፡ ናት ፡ በአካይያ ፡ ቆሮንቶስ ፡ እንዳለች ፡ በመላዋ ፡ መቄዶንያ ፤ መዲናዋ ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ትባላለች ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ከዚህ ፡ ገብቶ ፡ ጌታ ፡ ከፅንስ ፡ ጀምሮ ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፤ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፤ የሠራውን ፡ ትሩፋት ፡ ቢነግራቸው ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወደአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለሱ ፡ አመኑ ፡ ተጠመቁ ፡ ትምህርት ፡ ካልደረሰበት ፡ ለማዳረስ ፡ ወጥቶ ፡ ከሔደ ፡ በኋላ ፡ ሲያስተምር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ደረሰ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩ ፡ አይሁድ ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡበት ፡ በሉስዮስ ፡ ዳኝነት ፡ ያዙት ፡ ከዚያም ፡ ከፊልክስ ፡ ዘንድ ፡ ይወርዳል ፡ በፊልክስ ፡ እጅ ፡ ፪ ፡ ዓመት ፡ ይታሰራል ። ፊልክስ ፡ ተሽሮ ፡ ፊስጦስ ፡ ሲሾም ፡ ሮም ፡ በመጋቢያ ፡ ይወርዳል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ገብተው ፡ ወንጌል ፡ እንበለ ፡ ኦሪት ፤ ጥምቀት ፡ እንበለ ፡ ግዝረት ፤ አትረባም ፡ አትጠቅምም ፡ ብለዋቸዋል ። ይንደደው ፡ ይቈጨው ፤ ማን ፡ ከማን ፡ ሰንፎ ፡ ብለው ፡ ያስተማሩም ፡ አሉ ። ጳውሎስ ፡ ትምህርት ፡ በመፈታቱ ፡ እንጂ ፡ በመታሰሩ ፡ አያዝንም ፡ ብለው ፡ ያስተማሩም ፡ አሉ ። ሕዝቡም ፡ ሳይበቁ ። ዲቁና ፡ ዲያቆናቱ ፡ ሳይበቁ ፡ ቅስና ፡ ተመኝተዋል ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ለዚህ ፡ ይጽፋል ፡ ወእፈቅድ ፡ አኃዊነ ፡ ታእምሩ ፡ ዜናየ ፡ ከመ ፡ ፈድፋደ ፡ ተሰዐለ ፡ ውስተ ፡ ትምህርተ ፡ ወንጌሉ ፡ ለክርስቶስ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፪ ።)

በ ፡ እለ ፡ በቅንዓቶሙ ፡ ወበ ፡ እለ ፡ በተታሕዎቶሙ ፡ ወበ ፡ እለ ፡ ፈቀዱ ፡ ይስብኩ ፡ በፍቅር ፡ ሠናይ ፡ ወይምሀሩ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ይላል ፡ ቍ ፡ ፲፯ ፡ ወናሁ ፡ ተፈሣሕኩ ፡ በዝንቱ ፡ ወእትፌሣሕኒ ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ በኵሉ ፡ ምክንያት ፡ ይንግሩ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ እመኒ ፡ በአድልዎ ፡ ወእመኒ ፡ በእማን ፡ (ቍ ፡ ፲፰ ።)

ኵልከሙ ፡ ፍጹማን ፡ ዘንተ ፡ ሐልዩ ፡ ለነሂ ፡ ዘከመ ፡ ገብረ ፡ ለነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘወአቱ ፡ አርአያሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አኮ ፡ ሐይዶ ፡ ዘኮነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላ ፡ አትሒቶ ፡ ርእሶ ፡ ነሥአ ፡ አርአያ ፡ ገብር ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፭ ።)

ወእትአመን ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ እፌንዎ ፡ ለከሙ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ይላል ፡ (ቍ ፡ ፲፱)

ኵልከሙ ፡ ፍጹማን ፡ ዘንተ ፡ ሐልዩ ፡ ወለእመኒዐ ፡ ባዕድ ፡ ዘትሔልዩ ፡ ኪያሁኒ ፡ ይከሥት ፡ ለከሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ (ም ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።)

አስተበቍዓከሙ ፡ ኤዎድያን ፡ ወሰንጣኪን ፡ ከመ ፡ ተሐልዩ ፡ ለተልእኮ ፡ እግዚእነ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፪) ።
አስተበቍዓከ ፡ ለከ ፡ እኁየ ፡ ወመጸምርትየ ፡ ሰትረካ ፡ (ቍ ፡ ፫) ።
ወአምላኪየ ፡ ይፈጽም ፡ ለከሙ ፡ ኵሎ ፡ መፍቅደከሙ ፡ በከመ ፡ ብዕለ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ብሎ ፡
(ም ፡ ፬ ፡ ፲፩) ።
ወፈድፋደሰ ፡ እለ ፡ እምሰብአ ፡ ቄሣር ፡ ቤተ ፡ ንጉሥ ፡ ይላል ፡ (ም ፬ ፡ ፳፪) ።
የጻፈበት ፡ ሮም ፡ ከታብ ፡ ወላጅ ፡ አፍሮዲጡ ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፡ እምጳውሎስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡ አግብርተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አገልጋዮች ፡ ከምንኾን ፡ ከጳውሎስና ፡ ከጢሞቴዎስ ፡ የተላከ ች ፡ መልእክት ፡ (ሐተታ ) ፡ እንዳለፈው ።
ለኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ ተቀደሱ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምነው ፡ ከኢአማንያን ፡ ለተለዩ ፡ ከንዴት ፡ ለከበሩ ፡ ከኃጢአት ፡ ለነጹ ፤ በሃይማኖት ፡ ለጸኑ ፡ ሰዎች ፡ ትድረስ ።
እለ ፡ ሀለዉ ፡ ፊልጵስዮስ ፡ ምስለ ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፰) ።
ከቀሳውስት ፡ ከዲያቆናት ፡ ጋራ ፡ በፊልጵስዮስ ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ ትድረስ ፡ (ሐተታ ፡) ይህች ፡ ፊልጵስዮስ እንደቆራጣ ፡ እንደዋልድባ ፡ እንደዋጊና ፡ እንደወርቅ ፡ ለብሐ ፡ ቀሳውስት ፡ ዲያቆናት ፡ የበዙባት ፡ ሀገር ፡ ናትና ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ምስለ ፡ ቀሳውስት ፡ አለ ። አንድም ፡ ትብጻሕ ፡ ምስለ ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ለቀሳውስት ፡ ለዲያቆናት ፡ አስይዞ ፡ ለደ.ታልና ።
አንድም ፡ ( ትብጻሕ ፡ ለቀሳውስት ፡ ወለዲያቆናት ፡ ) ሕዝቡ ፡ ሳይበቁ ፡ ዲቁና ፡ ዲያቆናቱ ፡ ሳይበቁ ፡ ቅስና ፡ ተመኝተዋልና ፡ በፍና ፡ ተግልቆ ፡ ትብጻሕ ፡ ለቀሳውስት ፡ ወለዲያቆናት ፡ አለ

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፡ ሰላም ፡ ለክሙ ፡ ቸር ፡ አላችሁን ።
ወጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፯ ።)
የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ጸጋው ፡ ይደርባችሁ ፡ ይደረግላችሁ ።

፫ ፡ አአኰቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘልፈ ፡ በኵሉ ፡ ተዝካርክሙ ፡ ኪያየ ፡ (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፰ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፬)።
ኹልጊዜ ፡ እኔን ፡ በማሰባችሁ ፡ መምህርን ፡ እንጂ ፡ ማሰብ ፡ ትምህርትን ፡ አስመዘንጋት ፡ ነው ፡ ብዬ
እግዚአብሔርን ፡ አመሰግነዋለሁ ።

፬ ፡ ወእጼሊ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ በእንቲአክሙ ።
ኹልጊዜ ፡ ስለናንተ ፡ እጸልያለሁ ።
ወእገብር ፡ ጸሎተ ፡ ፍሥሐ ።
የደስታ ፡ ጸሎት ፡ እጸልያለሁ ፡ (ሐተታ) ፡ ጸሎተ ፡ ፍሥሐ ፡ ጸሎተ ፡ አኰቴት ፡ ጸሎተ ፡ አስተስርዮ ፡
አለና ።
ጸሎተ ፡ ፍሥሐ ፡ ተፈሣሕኩ ፡ ተፈሥሑ ፡ የሚለው ፡ ነው ።
ጸሎተ ፡ አኰቴት ፡ አአኵቶ ፡ ነአኵቶ ፡ የሚለው ፡ ነው ።
ጸሎተ ፡ አስተስርዮ ፡ ትንዝሐኒ ፡ በአዛብ ፡ ወእነጽሕ ፡ የሚለው ፡ ነው ።
በጢሞቴዎስ ፡ ይስረይ ፡ ሎሙ ፡ ብሎ ፡ የሚያመጣው ፡ ይሆናል ።

፭ ፡ በእንተ ፡ ተሳትፎትክሙ ፡ ኪያየ ፡ በትምህርተ ፡ ወንጌል ፡ አምቀዳሚት ፡ ዕለት ፡ እስከ ፡ ይእዜ ።
ከጥንተ ፡ ስብከት ፡ ጀምሮ ፡ እስከዛሬ ፡ በወንጌል ፡ ትምህርት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ስለኾናችሁ ። እን
ድም ፡ እኔን ፡ ስለመሰላችሁ ።

፮ ፡ እትአመን ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዘወጠነ ፡ ለክሙ ፡ ግብረ ፡ ሠናየ ፡ ውእቱ ፡ ይፌጽም ፡ ለክሙ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፲ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፯-፰ ።)
ውእቱና ፡ ውእቱ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስከሚመጣበት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡
ምጽአት ፡ እሱ ፡ የጀመረውን ፡ እንዲፈጽምላችሁ ፡ አምናለሁና ። አንድም ፡ እየራሱ ፡ ለማውጣት ፡ እሱ ፡
የጀመረውን ፡ እሱ ፡ እንዲፈጽምላችሁ ፡ አምናለሁና ።

፯ ፡ እስመ ፡ ርቱዕ ፡ ሊተ ፡ ዘንተ ፡ አሐሊ ፡ በእንቲአክሙ ።
ስለናንተ ፡ ይህን ፡ ማሰብ ፡ የሚገባኝ ፡ ስለኾነ ።
እስመ ፡ ሀሎክሙ ፡ ውስተ ፡ ልብየ ፡ ብመዋቅሕትየ ። (ኤፌ ፡ ፫ ፡ ፩ና ፡ ፬ ፡ ፩) ።
በእስራት ፡ ሳለሁ ፡ በሠራችሁልኝ ፡ ሥራ ፡ በልቡናዬ ፡ አላችሁ ። (አለ) ፡ ታውቃችኋልና ።
ወበቅሥትየ ።
በአፍአኒ ፡ ቀትል ፡ ወመንሡት ፡ ወበውስጥኒ ፡ ፍርሃት ፡ ባለው ።
ወበትምህርተ ፡ ጽድቅ ።
ወኢተአጽወተኒ ። ዛቲ ፡ ፍሥሐየ ፡ በደወለ ፡ አካይያ ፡ እስመ ፡ ጽድቁ ፡ ስክርስቶስ ፡ ይሄሉ ፡ ምስሌየ ፡
ባለው ፡ በሠራችሁልኝ ፡ ሥራ ፡ ታውቃችኋልና ።
እስመ ፡ ኅበርክሙ ፡ ምስሌየ ፡ በጸጋ ።
በጸጋ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ኾናችኋልና ፡ እናንተ ፡ በመስጠት ፡ እኔ ፡ በመቀበል ። አንድም ፡ በጸሎት ።

፰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማዕትየ ፡ ከመ ፡ አፈቅረክሙ ፡ በፍቅረ ፡ ክርስቶስ ።
ደቂቅየ ፡ ተፋቀሩ ፡ ባላት ፡ ፍቅር ፡ እንድወዳችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስክሬ ፡ ነው ።

፱ ፡ ወእጼሊ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ።
ስለዚህም ፡ እጸልያለሁ ።
ከመ ፡ ይብዛኅ ፡ ወይፈድፍድ ፡ ተፋቅሮትክሙ ።
ሃይማኖታችሁ ፡ ይጸናላችሁ ፡ ፍቅራችሁ ፡ ይበዛላችሁ ፡ ዘንድ ።
በአእምሮ ፡ በፈሊጥ ።
ወበኵሉ ፡ ጥበበ ፡ መንፈስ ፡ (ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፰ ።)
በልቡና ፡ ዕውቀት ፡ ኾናችሁ ።

፲ ፡ ከመ ፡ ትፍትኑ ፡ ወታመክሩ ፡ ዘይኄይስ ፡ ወዘይሜኒ ፡ ግብረ ።
የሚሻለውን ፡ በጐውን ፡ ግብር ፡ መርምራችሁ ፡ ትይዙ ፡ ዘንድ ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ትኩኑ ፡ ቅዱሳነ ፡ ዘእንበለ ፡ ዕቅፍት ፡ በዕለተ ፡ ክርስቶስ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ፡ ፩ ፡ ተሰ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ።)
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚመጣበት ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ መነቀፍ ፡ ሳይኖርባችሁ ፡ ትገኙ ፡ ዘንድ ።

፲፩ ፡ እንዘ ፡ ምሉአን ፡ አንትሙ ፡ ፍሬ ፡ ጽድቅ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ዛሬ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አብነት ፡ ፍሬ ፡ ትሩፋትን ፡ ተመልታችሁ ።
ለስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ።
ጌትነቱን ፡ ለማገልገል ።
ወአኰቴቱ ፡ (ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፱) ።
እሱን ፡ ለማመስገን ፤ ትኩኑ ፡ ዘእንበለ ፡ ዕቅፍት ፡ ሳለው ።
አንድም ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰጪነት ፡ ፍሬ ፡ ክብርን ፡ ተመልታችሁ ፡ ክብሩን ፡ ለመውረስ ፡ በሱ ፡ ቃል ፡ ለመመስገን ፡ መነቀፍ ፡ ሳይኖርባችሁ ፡ ንጹሓን ፡ ክቡራን ፡ ኹናችሁ ፡ ትገኙ ፡ ዘንድ፡ እጸሊ፡

## ክ ፍ ል ፡ ፪ ።

፲፪ ፡ ወእፈቅድ ፡ አኃዊነ ፡ ታአምሩ ፡ ዜናየ ፡ ከመ ፡ ተለዓለ ፡ ውስተ ፡ ትምህርተ ፡ ወንጌሉ ፡ ለክርስቶስ ፡ (፪ ፡ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፱ ።)
ወንድሞቻችን ፡ የኔም ፡ ነገር የወንጌል ትምህርት ፡ በደረሰበት ፡ ኹሉ፡ ደርሶ እንደታወቀ፡ ልታውቁ፡ እወዳለሁ ።

፲፫ ፡ ወተዐውቀ ፡ መዋቅሕትየ ፡ በክርስቶስ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ ምኲናን ፡ ወበኀበ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ (ም ፡ ፱፡፳፱)
በክርስቶስ ፡ ስም ፡ የሚኾን ፡ እስራቴም ፡ በገዥው ፡ በተገዥው ፡ ዘንድ ፡ እንደታወቀ ፡ ልታውቁ ፡፡ እወዳለሁ ።

፲፬ ፡ ወከመ ፡ ብዙኃን ፡ እምአኃዊነ ፡ ምእመናን ፡ በእግዚእነ ፡ ተዐገሡ ፡ በመዋቅሕትየ ፡ (ኤፌ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ። ፩ ፡ ተሰሎ ፡ ፫ ፡ ፫ ።)
በጌታችን ፡ ካሙኑ ፡ ከወንድሞቻችን ከምእመናን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በእስራት ፡ ሳለሁ ፡ የተቀበልሁትን ፡ መከራ ፡ ታግሠው ፡ እንደተቀበሉ ፡ ልታውቁ፡ ፡ እወዳለሁ ።
ወፈድፋደ ፡ ተሀበሉ ፡ ይንግሩ ፡ እኖቢያሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘእንበለ ፡ ፍርሃት ። (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፲፯)።
ይልቁንም ፡ እሱን ፡ ያገኘ ፡ ያገኘናል ፡ ሳይሉ ፡ ደፍረው ፡ ወንጌልን ፡ ሊያስተምሩ ፡ እንደወደዱ ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለሁ ።
፲፭ ፡ ቦ ፡ እለ ፡ በቅንዓቶሙ ። ይንደደው ፡ ይቈጨው ፡ ብለው ።
ወቦ ፡ እለ ፡ በተቃሕዎቶሙ፡
ማን ፡ ከማን ፡ ሰንፎ ፡ ብለው ፡ ያስተማሩ ፡ አሉ ።
ወቦ ፡ እለ ፡ ፈቀዱ ፡ ይስብኩ ፡ በፍቅር ፡ ሠናይ ፡ወይምሀሩ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ።
ጳውሎስ ፡ ትምህርት ፡ በመፈታቱ ፡ ነው ፡እንጂ ፡ በመታሰሩ ፡ አያዝንም ፡ ብለው ፡ በበጎ ፡ ፍቅር ፡ ያስተማሩም ፡ አሉ ።

፲፮ ፡ እስመ ፡ የአምሩ ፡ ከመ ፡ ሰምህሮ ፡ ወንጌል ፡ ተሠየምኩ ፡ ዓዲ ።
ዳግመኛ ፡ ወንጌልን ፡ ለማስተማር ፡ እንደተሾምሁ ፡ ያውቃሉና ፤ ዓዲ ፡ ለሐዋርያት ፡ ነው ።

፲፯ ፡ ወእለሰ ፡ በትዝኀርቶሙ ፡ ይንግሩ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ።
የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ይንደደው ፡ ይቈጨው ፤ ማን ፡ ከማን ፡ ሰንፎ ፡ ብለው ፡ የሚያስተምሩ ፡ ቢጽ ፡ሐሳውያን ፡ ግን ።
አኮ ፡ በንጽሕ ።
ክርርቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፤ ከማለት ፡ ተከልክለው ፡ አይደለም ። አንድም ፡ እንበላበት ፡ እንጠጣበት ፡ ከማለት ፡ ተከልክሰው ፡ አይደለም ።
ዳዕሙ ፡ ይትሐዘቡ ፡ ከመ ፡ ገቢሮሙ ፡ ኪያሁ ፡ ይወስኩ ፡ ሊተ ፡ ሕማመ ፡ በመዋቅሕትየ ። ቀ ፡ ፲፯ ።)
ይህን ፡ አድርገው ፡ በእስራት ፡ ሳይ ፡ ኀዘን ፡ ሊያጸኑብኝ ፡ ይወዳሉ ፡ እንጂ ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፰ ፡ ወናሁ ፡ ተፈሣሕኩ ፡ በዝንቱ ።
ጳውሎስ ፡ ትምህርት ፡ በመፈታቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመታሰሩ ፡ አያዝንም ፡ ብለው ፡ በፍቅር ፡ በማስተ
ማራቸው ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ ።
ወእትፌሣሕኒ ፡ ቦቱ ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።)
ይንደደው ፡ ይቈጨው ፡ ማን ፡ ከማን ፡ ሰንፎ ፡ ብለው ፤ ማስተማራቸውም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።
ከመ ፡ በኵሉ ፡ ምክንያት ፡ ይንግሩ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ።
በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ለማስተማር ፡ ነውና ።
እመኒ ፡ በእድልዎ ።
ይንደደው ፡ ይቈጨው ፤ ማን ፡ ከማን ፡ ሰንፎ ፡ ብለውም ፡ ቢኾን ።
ወእመኒ ፡ በእማን ።
ጳውሎስ ፡ ትምህርት ፡ በመፈታቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመታሰሩ ፡ አያዝንም ፡ ብለውም ፡ ቢኾን ፡ የክር
ስቶስን ፡ ስም ፡ ለማስተማር ፡ ነውና ።
ወይጸውዑ ፡ ኀቤሁ ፡ ሰብአ ።
ሰውንም ፡ ኹሉ ፡ ወደሱ ፡ ለመመለስ ፡ ነውና ፡ እትፌሣሕኒ ፡ ቦቱ ፡

፲፱ ፡ ወእነ ፡ እአምር ፡ ከመ ፡ ዛቲ ፡ ግብር ፡ ታበጽሐኒ ፡ ኀበ ፡ ሕይወት ፡ በጸሎትክሙ ፡ ወበሀብተ ፡ መንፈሱ ፡
ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።)
ይህች ፡ ትዕግሥት ፡ አለመቃናት ፡ በናንተ ፡ ጸሎት ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰጭነት ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡
እንድታደርሰኝ ፡ አው ቃለሁ ።

፳ ፡ በከመ ፡ ተሰፈውኩ ፡ ወተወከልኩ ፡ ከመ ፡ ኢይትኃፈር ፡ ወኢበምንትኒ ።
በምንም ፡ በምን ፡ ክብር ፡ እንዳላጣ ፡ እምኜ ፡ ተስፋ ፡ አድርጌ ፡ እንዳለሁ ፡ መጠን ።
ዳዕሙ ፡ ገሃደ ፡ በፍሥሓ ፡ መንፈስ ፡ ከመ ፡ ዘልፍ ።
ቀድሞ ፡ ሳልታሰር ፡ እናንተን ፡ አስተምሬ ፡ ዋጋዬን ፡ አገኛለሁ ፡ በማለት ፡ በልቡና ፡ ደስታ ፡ እንደ
ነበርሁ ፤ ዛሬም ፡ ታስሬ ፡ እናንተን ፡ አስተምሬ ፡ ዋጋዬን ፡ አገኛለሁ ፡ በማለት ፡ በልቡና ፡ ደስታ ፡ አለሁ ፡
እንጂ ። ኢይትኀፈር ።

ወይእዜኒ ፡ ዕበዩ ፡ ለክርስቶስ ፡ በሥጋየ ።
(ዕበዮ ፡ ሲል ፡ ነው ፡) እጸውር ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ዛሬም ፡ የክርስቶስን ፡ መከራውን ፡ በሥጋዬ ፡ እቀበላለሁ
እመኒ ፡ በሕይወትየ ።
በሕይወቴም ፡ ቢኾን ፡ (አለ) ፡ እጁን ፡ እግሩን ፡ ታስሮ ፡ ነውና ።
ወእመኒ ፡ በሞትየ ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፲፮) ።
በሞቴም ፡ ቢኾን ፡ (አለ ፡) በሰይፍ ፡ ይሞታልና ።
(አንድም ፡) ወእነ ፡ እአምር ፡ ከመ ፡ ዛቲ ፡ ግብር ፡ ታበጽሐኒ ፡ ኀበ ፡ ሕይወት ፡ በጸሎትክሙ ፡ ወበሀብተ ፡
መንፈሱ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ይህች ፡ ትዕግሥት ፡ አለመቃናት ፡ በናንት ፡ ጸሎት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰጭነት ፡ ወደሕይወት ፡ እን
ድታደርሰኝ ፡ አውቃለሁ ።
በከመ ፡ ተሰፈውኩ ፡ ወተወከልኩ ፡ ከመ ፡ ኢይትኀፈር ፡ ወኢበምንትኒ ፡ (ወበከመ ፡ ተወከልኩ ፡)
በምንም ፡ በምን ፡ ክብር ፡ እንዳላጣ ፡ እምኜ ፡ ተስፋ ፡ አድርጌ ፡ እንዳለሁም ፡ ኹሉ ፡
ዳዕሙ ፡ ገሃደ ፡ በፍሥሓ ፡ መንፈስ ፡ ከመ ፡ ዘልፍ ።
ዛሬ ፡ ታሥሬ ፡ እናንተን ፡ አስተምሬ ፡ ዋጋዬን ፡ እገኛለሁ ፡ በማለት ፡ በልቡና ፡ ደስታ ፡ እንዳለሁ ፡
እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ተፈትቼ ፡ እናንተን ፡ አስተምሬ ፡ ዋጋዬን ፡ አገኛለሁ ፡ በማለት ፡ በልቡና ፡ ደስታ ፡
አለሁ ፡ እንጂ ፡ በምንም ፡ በምን ፡ ክብር ፡ እንዳላጣ ፡ እምኜ ፡ ተስፋ ፡ አድርጌ ፡ እንዳለሁ ፡ ኹሉ ።
ወይእዜኒ ፡ ዕበዩ ፡ ለክርስቶስ ፡ በሥጋየ ።
ዛሬ ፡ የክርስቶስ ፡ ክብሩ ፡ በኔ ፡ አለ ።
እመኒ ፡ በሕይወትየ ።
በሕይወቴም ፡ ቢኾን ፡ (አለ ፡) ወከብረት ፡ ነፍሰሙ ፡ በውስተ ፡ ዓለማት ፡ ክልኤቲ ፡ ዘዝየ ፡ ወዘከሃ ፡
እንዲል ፡ (መቅ ፡ ዉን ፡) በወዲሁ ፡ አማልክት ፡ ተመሰሉ ፡ ሰብእ ፡ ወወረዱ ፡ ኀቤነ ፡ ይላቸዋልና ፡ (ግብ ፡ ሐዋ
፲፬ ፡ ፲፩ ።)

www.ethiopianorthodox.org

ወእሙኒ ፡ በሞትየ ።

በሞቴም ፡ ቢኾን ፡ (እስ ፡) ወሀሎ ፡ ይትዌሰክ ፡ ሥን ፡ በዲበ ፡ ሥን ፡ እንዲል ፡ (እፌ ፡ ወር)፣ በወዲያው ተወሰኮ ፡ ዘነግእያን ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ እያቋርጥምና ፡ እንትሙ ፡ ትነብሩ ፡ ዲበ ፡ ዐውርቱ ፡ ወከልኤቱ ፡ መናብርት ፡ ብሏችዋልና ።

፳፩ ፡ እንሰ ፡ እሙኒ ፡ ሐየውኩ ፡ ለክርስቶስ ።

እኔስ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋም ፡ ብኖር ፡ ክርስቶስን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።

ወእሙኒ ፡ ሞትኩ ፡ ርቡሕ ፡ ሊተ ፡ (ገላትያ ፡ ፩ ፡ ፳ ።)

ብሞትም ፡ ዋጋዬ ፡ ይቆየኛል ።

፳፪ ፡ ወሰእሙኒ ፡ ሐየውኩ ፡ በሥጋየ ፡ ከመ ፡ እፍረይ ፡ በምግባርየ ።

በሕይወተ ፡ ሥጋም ፡ ብኖር ፡ ፍሬ ፡ ትሩፋትን ፡ እፈራ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ኃጣእኩ ፡ ዘእኀሪ ፡ ለነፍስየ ፡ እምእሉ ፡ ክልኤቱ ፡ ዘያጽሕቀኒ ፡ ፈቂዶቶሙ ፡ (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።)

እሳቸውን ፡ ከሚያሻኝ ፡ ከሊሁ ፡ ከኹለቱ ፡ ለሰውነቴ ፡ የምመርጠው ፡ ቸገረኝ ።

፳፫ ፡ እፈቱስ ፡ እፍልስ ፡ ወእትፈለጥ ፡ እምዓለም ፡ ከመ ፡ እሀሉ ፡ ኀበ ፡ ክርስቶስ ።

መውደዱንስ ፡ ከዚሁ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ተለይቼ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ልኖር ፡ እወዳለሁ ።

ወፈድፋደ ፡ ይኄይስ ፡ ወይደሉ ፡ ሊተ ፡ ዝንቱ ። (፩ ፡ ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፬ ፡ ፱ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፰ ።)

ይልቁንም ፡ ይህ ፡ ይሻላል ፡ (እለ ፡) በሞት ፡ መለየቱ ።

፳፬ ፡ ወከመ ፡ እህሉ ፡ ዓዲ ፡ በሕይወቱ ፡ ሥጋየ ፡ ርቱዕ ፡ በእንቲአክሙ ።

ወዲህም ፡ ስለናንት ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ መኖር ፡ ይገባኛል ።

፳፭ ፡ ወእትአመን ፡ እእሚርየ ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ እነብር ፡ ወእሄሉ ፡ ለፍሥሓክሙ ፡ ወለተልዕሎ ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፳፬ ።)

ደስታችሁ ፡ እንዲበዛላችሁ ፤ ሃይማኖታችሁ ፡ እንዲጸናላችሁ ፤ (እእሚርየ ፡) ይህን ፡ እውቄ ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ እንድኖር ፡ እምናለሁ ፡ ልኖር ፡ እወዳለሁ ።

፳፮ ፡ ከመ ፡ እመ ፡ መጻእኩ ፡ ካዕበ ፡ ኀቤክሙ ፡ ይዕበይ ፡ ወይትወሰክ ፡ ክብርክሙ ፡ በላዕሌየ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ወደናንት ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ በኔ ፡ በትምህርት ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰጪነት ፡ ክብር ፡ ይበዛላችሁ ፡ ዘንድ ።

፳፯ ፡ ወበዘይደሉ ፡ ለትምህርተ ፡ ክርስቶስ ፡ ይኩን ፡ ዳዕሙ ፡ ግብርክሙ ፡ (ቈላ ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ፩ ፡ ተሰሎ ፡ ፪ ፡ ፲፪)

ሥራችሁም ፡ ለክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ ለወንጌል ፡ በሚገባ ፡ ብቻ ፡ ይኹን ፡ (ይኹን ፡ እንጂ) ።

ወለእመ ፡ መጻእኩ ፡ ኀቤክሙ ፡ እሬኢ ፡ ዘንተ ።

ወደናንት ፡ ብመጣም ፡ ይህን ፡ እያለሁ ።

ወእመኒ ፡ እንዘ ፡ ኢሀሎኩ ፡ እሰምዕ ፡ በላዕሌክሙ ።

ባልመጣም ፡ እሰማለሁ ፡ እትእመን ፡ ላለው ፡ ዋዌ ።

እንድም ፡ ብመጣ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ባልመጣም ፡ እሰማ ፡ ዘንድ ፡ ይዕበይ ፡ ወይትወሰክ ፡ ክብርክሙ ፡ ላለው ፡ ዋዌ ።

እንድም ፡ ብመጣ ፡ እንዳይ ፡ ልኹን ፤ ባልመጣ ፡ እንድሰማ ፡ ልኹን ፡ ዳዕሙ ፡ ይኩን ፡ ግብርክሙ ፡ ላለው ፡ ዋዌ ።

ከመ ፡ ትቀውሙ ፡ በእሐዱ ፡ መንፈስ ፡ ወበእሐዱ ፡ ነፍስ ።

እንዳንድ ፡ ልብ ፡ መካሪ ፡ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ኾናችሁ ፡ ጸንታችሁ ፡ እንዳላችሁ ፡ እንዳይ ፡ ልኹን ፡ እንድሰማ ፡ ልኹን ።

ወእንዘ ፡ ትትጋደሉ ፡ በጻማ ፡ ሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ፲፰ ።)

ሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ ባመጣው ፡ ፃር ፡ እየፃራችሁ ።

፳፰ ፡ ወእንዘ ፡ ኢያንቀለቅሉክሙ ፡ በምንትኒ ፡ እለ ፡ ይትቃወሙነ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፬ ።)

የሚቃወሙን ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ በምንም ፡ በምን ፡ ሳያንዋውጧችሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ሕርትምናሆሙ ።
ጥፋታቸው ፡ ተርታነታቸው ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ እስኪታወቅ ፡ የሚቃወሙን ።
ወለከሙሰ ፡ ሕይወት ።
ለናንት ፡ ግን ፡ (ሕይወት ፡) ልጅነት ፡ አላችሁ ።
፳፱ ፡ ወዘንተኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘጸገወክሙ ፡ አኮ ፡ ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ ትእመኑ ፡ ቦቱ ።
ይህንም ፡ (ሕይወት ፡) ልጅነት ፡ የሰጣችሁ ፡ እምናችሁበት ፡ ብቻ ፡ ልትኖሩ ፡ አይደለም ።
አላ ፡ ዓዲ ፡ ከመኒ ፡ ትሕምሙ ፡ በእንቲአሁ ፡ (ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፫ ።)
በሱ ፡ ስላመናችሁ ፡ እሱን ፡ አብነት ፡ ስላደረጋችሁ ።
፴ ፡ ወከማሁ ፡ ከመ ፡ ትትጋደሉ ።
እንደሱ ፡ መከራም ፡ ልትቀበሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ዘከመ ፡ ርኢክሙኒ ፡ ኪያየ ፡ ወሰማዕክሙ ፡ በእንቲአየ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፯ ፡ ፳፱ ፤ ቈላ ፡ ፩ ፡ ፳፱ ።)
ቀድሞ ፡ የኔን ፡ ነገር ፡ እንዳያችሁ ፡ የኔን ፡ ነገር ፡ እንደሰማችሁ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፡ ወእምከመ ፡ ሀለወ ፡ ኀቤክሙ ፡ ይእዜ ፡ ፍሥሐ ፡ በክርስቶስ ።
በክርስቶስ ፡ እምና ፡ የሚገኘውን ፡ ተስፋ ፡ የያዘ ፡ አእምሮ ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ካለ ።
አው ፡ ዘይናዝዝ ፡ ልበ ፡ በተፋቅሮ ።
በፍቅር ፡ ልቡናን ፡ የሚያጸና ፡ (አእምሮ) ።
አው ፡ ዘይሳተፍ ፡ በመንፈስ ። (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ ፫ ።)
በልቡና ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ።
አው ፡ በምሕረ ፡ ወተማህሎ ።
ለሰው ፡ በማዘን ፡ በመራራት ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፡ አእምሮ ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ካለ ።
፪ ፡ ፈጽሙ ፡ ሊተ ፡ ፍሥሐየ ።
ደስታዬን ፡ ፈጽሙልኝ ።
ከመ ፡ ተሐልዩ ፡ ኪያሁ ።
ያኑ ፡ ብቻ ፡ ታስቡ ፡ ዘንድ ።
ወተሀልዉ ፡ በተፋቅሮ ፡ በአሐዱ ፡ ነፍስ ፡ ወበአሐዱ ፡ ምክር ። (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፲፯ ፤ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲ ።)
እንዳንድ ፡ ልብ ፡ መካሪ ፡ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ኾናችሁ ፡ በፍቅር ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ።
ወእምከመ ፡ ሀለወ ፡ ኀቤክሙ ፡ ይእዜ ፡ ፍሥሐ ፡ በክርስቶስ ።
አንድም ፡ በክርስቶስ ፡ እምና ፡ የሚገኘውን ፡ ተስፋ ፡ የያዘ ፡ መምህር ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ቢኖር ።
አው ፡ ዘይናዝዝ ፡ ልበ ፡ በተፋቅሮ ።
ልቡናን ፡ በፍቅር ፡ የሚያጸና ።
አው ፡ ዘይሳተፍ ፡ በመንፈስ ።
በልቡና ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ።
አው ፡ በምሕረ ፡ ወበተማህሎ ።
ለሰው ፡ በማዘን ፡ በመራራት ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፡ መምህር ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ቢኖር ።
ፈጽሙ ፡ ሊተ ፡ ፍሥሐየ ።
እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ (ፈጽሙ ፡ ሊተ ፡ ፍሥሐየ) ፡ ደስታዬን ፡ ፈጸሙልኝ ።
ከመ ፡ ተሐልዩ ፡ ኪያሁ ።
ያኑ ፡ ብቻ ፡ እንድታስቡ ፡ ብትኾኑ ።
ወተሀልዉ ፡ በተፋቅሮ ፡ በ፩ ፡ ነፍስ ፡ ወበ፩ ፡ ምክር ።
እንዳንድ ፡ ልብ ፡ መካሪ ፡ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ኾናችሁ ፡ በፍቅር ፡ እንድትኖሩ ፡ ብትኾኑ ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ደስታዬን ፡ ፈጸሙልኝ ።
፫ ፡ ወኢትግበሩ ፡ በተቃሕዎ ።
የምትሠሩትን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ በሥጋዊ ፡ ፍክክር ፡ አታድርጉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወኢበአፍቅሮ ፡ ክብረ ፡ ከንቱ ።
ውዳሴ ፡ ከንቱን ፡ በመሻት ፡ አታድርጉ ።
ወኢትእበዩ ፡ አትታበዩ ፡ አትመኩ ።
አላ ፡ በትሑት ፡ ልብ ፡ አክብሩ ፡ ቢጸክሙ ፡ እምርእስክሙ ። (ገላትያ ፡ ፭ ፡ ፳፮ ፤ ሮሚ ፡ ፲፪ ፡ ፲ ።)
ትሕትናን ፡ በያዘ ፡ ልቡና ፡ ኾናችሁ ፡ ከራሳችሁ ፡ ይልቅ ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ አክብሩ ፡ እንጂ ።

፬ ፡ ወኢትጽሐቁ ፡ ለባሕቲትክሙ ።
የራሳችሁ ፡ ግዳጅ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ አትሹ ።
ዘእንበለ ፡ ለቢጽክሙ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፳፬ ፡ ፴፫ ።)
የወንድሞቻችሁ ፡ ግዳጅ ፡ የሚፈጸምበትንም ፡ እንጂ ።

፭ ፡ ዘለክሙ ፡ ፍጹማን ፡ ዘንተ ፡ ሐልዩ ።
በልደተ ፡ ነፍስ ፡ ፍጹም ፡ የምትኾኑ ። አንድም ፡ ሕዝቡ ፡ ሳይበቁ ፡ ዲቁና ፤ ዲያቆናቱ ፡ ሳይበቁ ፡ ቅስና ተመኝተዋልና ፡ በፍና ፡ ተሣልቆ ፡ ዘለክሙ ፡ ፍጹማን ፡ አለ ፡ ፍጹማን ፡ የምትኾኑ ፡ ኹላችሁም ፡ ይህን አስቡ ።
ለነሂ ፡ ዘከመ ፡ ገብረ ፡ ለነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። (ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ።)
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለኛ ፡ ያደረገልንን ፡ ነገር ፡ አስቡ ።

፮ ፡ ዘውእቱ ፡ አርአያሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።
በመልክ ፡ የሚመስለው ፡ በባሕርይ ፡ የሚተካከለው ።
አኮ ፡ ሀይዶ ፡ ዘኮነ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ዲያብሎስ ፡ ቀምቶ ፡ እንደአዳም ፡ ተመኝቶ ፡ አይደለም ።

፯ ፡ አላ ፡ አትሐቶ ፡ ርእሶ ፡ ነሥአ ፡ አርአያ ፡ ገብር ። (ቈላ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፲፯ ፡ ፭ ፡ ዘፍ ፡ ፫፡፭)
ራሱን ፡ አዋርዶ ፡ አርአያ ፡ ገብርን ፡ ቢነሣ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
አንድም ፡ አኮ ፡ ሀይዶ ፡ ዘኮነ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔርነት ፡ የሌለው ፡ ኾኖ ፡ እግዚአብሔር ፡ የኾነ ፡ አይደለም ።
አላ ፡ አትሐቶ ፡ ርእሶ ፡ ነሥአ ፡ አርአያ ፡ ገብር ።
የሌለውንስ ፡ አርአያ ፡ ገብርን ፡ ነሣ ፡ እንጂ ።
አኮ ፡ ሀይዶ ፡ ዘኮነ ፡ እግዚአብሔር ።
ሥጋ ፡ ተለውጦ ፡ አምላክ ፡ የኾነ ፡ አይደለም ።
አላ ፡ አትሐቶ ፡ ርእሶ ፡ ነሥአ ፡ አርአያ ፡ ገብር ።
ቃል ፡ ባሕርዩን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ አርአያ ፡ ገብርን ፡ ቢነሣለት ፡ ነው ፡ እንጂ ።
አንድም ፡ አኮ ፡ ሀይዶ ፡ ዘኮነ ፡ እግዚአብሔር ።
ቃል ፡ ተለውጦ ፡ ሥጋ ፡ የኾነ ፡ አይደለም ።
አላ ፡ አትሐቶ ፡ ርእሶ ፡ ነሥአ ፡ አርአያ ፡ ገብር ።
ባሕርዩን ፡ ባለው ፡ አጽንቶ ፡ አርአያ ፡ ገብርን ፡ ነሣ ፡ እንጂ ።
ወተመሰለ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ። (ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፫ ፡ ፯ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፱ ፤ ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯ ።)
በው ፡ ኾነ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ (አለ ፡) የሰውነት ፡ ሥራ ፡ ሠራ ።

፰ ፡ ወሰምዐ ፡ ወተአዘዘ ፡ እስከ ፡ በጽሐ ፡ ለሞት ።
እስከመሞት ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ እሺ ፡ በጂ ፡ አለ ።
ወሞቱሂ ፡ ዘበመስቀል ። (ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ፡ ፭ ፡ ፰ ።)
ሞቱም ፡ በመስቀል ፡ የኾነው ፡ ነው ። በመስቀል ፡ ነው ።

፱ ፡ ወበእንተዝ ፡ አዕበዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥቀ ።
ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጽሞ ፡ አከበረው ፡ (አለ ፡) ንበር ፡ በየማንየ ፡ አለው ።
ወጸገዎ ፡ ስመ ፡ ዘየዐቢ ፡ እምኵሉ ፡ ስም ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፪ ፡ ፴፫ ፤ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፳ ፡ ፳ ፡ ዕብ ፡ ፩ ፡ ፫ ፡ ፬ ።)
ክስም ፡ ኹሉ ፡ የበለጠ ፡ ስምን ፡ ሰጠው ፡ (አለ) ፡ አምላክ ፡ ወልድ ፡ እግዚእ ፡ መባልን ።
ሰምዓ ፡ ወተአዘዘ ፡ እስከ ፡ በጽሐ ፡ ለሞት ፡ ያለውና ፡ ወውእቱ ፡ ገብረ ፡ በሀላዊሁ ፡ በዘያነጽሕ ፡ ኃጢአተነ ፡ ያለው ፡ (ዕብ ፡ ፩ ፡ ፫ ፡) በእንተዝ ፡ አዕበዮ ፡ ያለውና ፡ ወነበረ፡በየማነ፡ ዕበዩ ፡ በሰማያት ፡ ያለው ፡ (ዕብ ፡ ፩፡)

www.ethiopianorthodox.org

፱ ፡ ጸገም ፡ ስመ ፡ ዘየዐቢ ፡ እምኵሉ ፡ ያለውና ፡ ወወረሰ ፡ ስመ ፡ ዘየዐቢ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ዕብ ፡ ፩ ፡ ፬)
፲ ፡ ከመ ፡ ለስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይስግድ ፡ ኵሉ ፡ ብርክ ፡ ዘበሰማያት ፡ ወዘበምድር ። (ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፳፫ ፡ ራእ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ፡ ኢሳ ፡ ፵፭ ፡ ፳፫ ።)

ብርክ ፡ መላእክት ፡ ብርክ ፡ ደቂቀ ፡ አዳም ፡ ኹሉ ፡ ለስሙ ፡ ይስግድ ፡ ዘንድ ።

ወበቀላያት ።

እመቤታችን ፡ በነገረ ፡ ማርያም ፡ ያየቻቸው ።

ወእለ ፡ ታሕተ ፡ ምድር ።

ካልእ ፡ ፍጥረት ፡ ናቸው ፡ ኹሉ ፡ ለስሙ ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ።

፲፩ ፡ ጸገም ፡ ስመ ፡ ዘየዐቢ ፡ ወኵሉ ፡ ልሳን ፡ ይግነይ ፡ ከመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእ ፡ በስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ። ( ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፪ ፡ ፴፮ ፡ ፲ ፡ ፴፮ ፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፳፫ ።)

አንደበት ፡ ኹሉ ፡ ኢየሱስ ፡ በአብ ፡ ጌትነት ፡ ያለ ፡ እግዚእ ፡ እንደኾነ ፡ ያምን ፡ ዘንድ ፡ ጸገም ።

፲፪ ፡ ወይእዜኒ ፡ አኃውየ ፡ በከመ ፡ ዘልፈ ፡ ትሰምዑኒ ።

አሁንም ፡ ወንድሞቼ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ እንደምትሰሙኝ ።

ወአኮ ፡ በሀልዎትየ ፡ ዳዕሙ ።

እኔ ፡ ባለሁበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ወዓዲ ፡ ፈድፋደ ፡ እንዘ ፡ ኢሀሎኩ ።

በሌለሁበትም ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ባለሁበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ኹሉ ፡ ጊዜ ፡ እንድትሰሙኝ ።

በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ፡ ተገበሩ ፡ ለሕይወትከሙ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ፡ መዝ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።)

በፍርሃት ፡ በረዓድ ፡ ኾናችሁ ፡ ድኅነት ፡ የምታገኙበትን ፡ ሥራ ፡ ሥሩ ።

፲፫ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ዘይረድእከሙ ፡ ፈቃዶ ።

ፈቃዱን ፡ ለማሠራት ፡ የሚረዳችሁም ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ወይፈጽም ፡ ለከሙ ፡ ግህሎ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፭ ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፭ ።)

ይቅርታውንም ፡ ይፈጽምላችሁ ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ፈቃዱን ፡ ለማሠራት ፡ የሚረዳችሁ ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ይፈጽም ፡ ለከሙ ፡ ) ይቅርታውን ፡ ይፈጽምላችሁ ።

፲፬ ፡ ወግበሩ ፡ ኵሎ ፡ ዘትገብሩ ፡ በተሰናዕዎ ፡ ወበሥምረት ፡ ዘእንበለ ፡ ነጐርጓር ፡ ወዘእንበለ ፡ ኑፋቄ ፡ ( ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፱ ። )

የምትሠሩትንም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ያለቂም ፡ ያለጥርጥር ፡ በፈቃድ ፡ በስምምነት ፡ ሥሩ ።

፲፭ ፡ ከመ ፡ ትኩኑ ፡ ንጹሓነ ፡ ወየዋሃነ ።

ንጹሓን ፡ ኾናችሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ኑፋቄ ፤ የዋሃን ፡ ኾናችሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ነጐርጓር ።

ከመ ፡ ውሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ም ፡ ፩ ፲ ።)

ውሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደመሆናችሁ ፡ እንደወሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደሐዋርያት ።

እንዘ ፡ እልብከሙ ፡ ነውር ፡ በማእከለ ፡ ውሉድ ፡ ዓላውያን ፡ ወግፍቱዓን ።

ድል ፡ ተነሥተው ፡ እፍን ፡ ጭፍን ፡ ብለው ፡ ወደኦሪት ፡ ወደኃጢአት ፡ በሔዱ ፡ በዓላውያን ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ መነቀፍ ፡ ሳይኖርባችሁ ።

ወታስተርእዩ ፡ ከመ ፡ ብርሃናት ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ፡ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፰ ።)

እንዲህ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ እንደጨረቃ ፡ እንደከዋክብት ፡ ትኾናላችሁ ። አንድም ፡ አንትሙ ፡ ብርሃኑ ፡ ለዓለም ፡ እንዳላቸው ፡ እንደነቢያት ፡ እንደሐዋርያት ፡ ትኾናላችሁ ።

፲፮ ፡ እንዘ ፡ ትሜህሩ ፡ ቃለ ፡ ሕይወት ።

ድኅነት ፡ የሚገኝበት ፡ ወንጌልን ፡ ስታስተምሩ ፡ ብተገኙ ፡ ታስተርእዩ ።

በዘእትሜካሕ ፡ አነ ፡ በዕለተ ፡ ክርስቶስ ። (፩ ተሰ ፡ ፪ ፡ ፲፱ ።)

ክርስቶስ ፡ በሚመጣበት ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ እኔ ፡ በምመካባችሁ ፡ ገንዘብ ፡ (እሰ) ፡ አኮኑ ፡ እግዚእ ፡ ሐምስ ፡ መካልየ ፡ ወሀብከኒ ፡ ወናሁ ፡ ሐምስ ፡ መካልይ ፡ ዲቢሆን ፡ ዘረባሕኩ ፡ ብዬ ፡ በምመካባችሁ ፡ ገንዘብ ።

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ፡ አኮ ፡ ለከንቱ ፡ ዘሮጽኩ ።
ዛሬ ፡ ያስተማርሁ ፡ ከንቱ ፡ አሪትን ፡ አይደለምና ፡ እንዘ ፡ ትሜህሩ ፡ ላለው ።
ወአኮ ፡ ለከንቱ ፡ ዘጻመውኩ ። (ኢሳ ፡ ፵፱ ፡ ፬ ፡ ገላ ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፱ ፡)
መከራ ፡ የተቀበልሁ ፡ ዋጋ ፡ ላለመቀበል ፡ አይደለምና ፡ በዘእትሜካህ ፡ እኑ ።

፲፯ ፡ ወአወጽሕ ፡ በእንተ ፡ መሥዋዕተ ፡ እምልኮ ፡ ለሃይማኖትክሙ ።
ሃይማኖታችሁ ፡ ሊጸናላችሁ ፡ ስለመገዛት ፡ መሥዋዕት ፡ ፈንታ ፡ የደም ፡ አረቂ ፡ ዕንባዬን ፡ አፈሳለሁ ።
እንድም ስለመገዛት ፡ መሥዋዕት ፡ ፈንታ ፡ የሚኾን ፡ የደም ፡ አረቂ ፡ ዕንባዬን ፡ አፈሳለሁ ፡ እንድም፡
ያፈሰስሁ ፡ አኮ ፡ ለከንቱ ።
ወናሁ ፡ እትፌሣሕ ፡ ወእትሐሠይ ፡ ለከሙ ፡ (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፮ ፡)
ያን ፡ ጊዜ ፡ (ብከሙ ) ፡ በናንት ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

፲፰ ፡ ወአንትሙኒ ፡ ተፈሥሑ ፡ ወተሐሠዩ ፡ ሊተ ። (ም ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፬ ፡ ፬ ፡)
(ብየ ፡ ) እናንተንም ፡ ዛሬ ፡ በኔ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ።

፲፱ ፡ ወእትአመን ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ እፌንዎ ፡ ለከሙ ፡ ለጢሞቴዎስ ።
ጢሞቴዎስን ፡ ወደናንተ ፡ እንድሰደው ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምናለሁ ።
ከመ ፡ እትፌሣሕ ፡ አነሂ ፡ ሰሚዕየ ፡ ዜናከሙ ።
እኔም ፡ የናንተን ፡ ነገር ፡ ሰምቼ ፡ ደስ ፡ ይለኝ ፡ ዘንድ ።

፳ ፡ እስመ ፡ አልብየ ፡ ዘከመ ፡ ግዕዝየ ፡ ዘእንበሌሁ ፡ ዘይጸውር ፡ ትካዘክሙ ፡ በአእምሮ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፯ ፡ ፲ ።)
እንደኔ ፡ ኾኖ ፡ በፈሊጥ ፡ ግዳጃችሁን ፡ የሚፈጽምልኝ ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለምና ። እንድም ፡ ጢሞ
ቴዎስን ፡ ወደናንት ፡ የሰደድሁት ፡ እንደኔ ፡ ኾኖ ፡ በፈሊጥ ፡ ግዳጃችሁን ፡ የሚፈጽምልኝ ፡ ሌላ ፡ የለምና
ስላልኖረ ፡ ነው ።

፳፩ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ትካዘ ፡ ርእሱ ፡ ይሔሊ ፡ ወአኮ ፡ ዘክርስቶስ ፡ (፪፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ።)
ኵልክሙ ፡ ትካዘ ፡ ርእስክሙ ፡ ትሔልዩ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እስመ ፡ ኰመዝ ፡ ልማዱ ፡ ለብፁዕ ፡ ጳውሎስ፡
ያመሠጥር ፡ ቃለ ፡ ነገር ፡ እንዲል ፡ (አፈ ፡ ወርቅ) ፡ አርቆ ፡ መናገር ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡(ሐተታ) ፡ጌታ ፡
በወንጌል ፡ ምንት ፡ ይሬስዮሙ ፡ እንዳለ ፡ እሬስየክሙ ፡ ሲል ። እፎ ፡ ናመስጥ ፡ ብሎ ፡ እንዲያመጣ ፡
ታመስጡ ፡ ሲል ፡ ከዚህም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ኹላችሁም ፡ የክርስቶስን ፡ ያይደለ ፡ የራሳችሁን ፡ ግዳጅ ፡
ለመፈጸም ፡ የምትሹ ፡ ስለኾነ ።

፳፪ ፡ ወተአምርዎ ፡ ግዕዞ ፡ ለዝንቱ ፡ ብእሲ ።
የዚያን ፡ ሰውም ፡ ግብሩን ፡ ታውቁታላችሁ ።
ዘከመ ፡ ተቀንየ ፡ ሊተ ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ ለወላዲሁ ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ )
ልጅ ፡ ለአባቱ ፡ እንዲገዛ ። እንድም ፡ ለአባቱ ፡ የሚገዛ ፡ ልጅ ፡ እንደመኾኑ ፡ በወንጌል ፡ ትምህርት፡
እንደተገዛልኝ ፡ ታውቃላችሁ ።

፳፫ ፡ ኪያሁ ፡ እሴፎ ፡ እፌንዎ ፡ ፍጡነ ።
እሱን ፡ ፈጥኜ ፡ ወደናንት ፡ እንድሰደው ፡ እምናለሁ ፡ ልሰደው ፡ እወዳለሁ ።
አእሚርየ ፡ ዘከመ ፡ ሀሎኩ ፡ እፈንዎ ፡ ሶቤሃ ። እፈነዎና ፡ እፌንዎ ፡ አንድ ፡ ወገን ።
የሱ ፡ መኖር ፡ የኔ ፡ መኖር ፡ እንደኾነ ፡ ዐውቄ ፡ እፈንዎ ።

፳፬ ፡ ወእትአመን ፡ በእግዚእነ ፡ ከመ ፡ አነሂ ፡ ፍጡነ ፡ እመጽእ ። (ም ፡ ፩ ፡ ፳፭ ።)
እኔም ፡ ፈጥኜ ፡ እንድመጣ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እምናለሁ ።

፳፭ ፡ ወይእዜሰ ፡ ፈድፋደ ፡ ጽህቁ ፡ በእንተ ፡ እፍሮዲጡ ፡ እኁነ ፡( ም ፡ ፬ ፡ ፲፰ ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፰ ፡ ፳፫ ።)
ዛሬ ፡ ግን ፡ ወንድማችን ፡ አፍሮዲጡን ፡ ልሰደው ፡ ወደድሁ ።
ዘየኀብር ፡ ግብረ ፡ ምስሌየ ።
ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚኾን ።
ወዓሊ ፡ ዘክርስቶስ ።
የክርስቶስ ፡ አገልጋይ ፡ የሚኾን ።

www.ethiopianorthodox.org

ወለክሙሰ ፡ ሐዋርያክሙ ።

ለእናንተ ፡ ግን ፡ መምህራችሁ ፡ የሚኾን ።

ወላእክየ ፡ ለትካዝየ ።

ለኔም ፡ ግዳጄን ፡ ለመፈጸም ፡ አገልጋዩ ፡ የሚኾን ።

እፌንዎ ፡ ለክሙ ።

ወደናንተ ፡ ልሰደው ፡ ወደድሁ ።

፳፮ ፡ እስመ ፡ ይጽህቅ ፡ ይርአይክሙ ፡ እእሚሮ ፡ ዘሰማዕክሙ ፡ ከመ ፡ ደወየ ።

እንደታመመ ።

ወበጽሐ ፡ ለሞት ።

ለሞት ፡ እንደደረሰ ፡ ሰምታችሁ ፡ እንዳዘናችሁለት ፡ ዐውቆ ፡ ሊያያችሁ ፡ ይወዳልና ።

፳፯ ፡ ወባሕቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሕሮ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እግዚእብሔር ፡ ይቅር ፡ አለው ።

ወእኮ ፡ ሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ።

ይቅር ፡ ያለውም ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

እዲ ፡ ሊተኒ ።

እኔንም ፡ ይቅር ፡ አለኝ ፡ እንጂ ።

እንድም ፡ ወእኮ ፡ ሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ።

ያዘነለትም ፡ ለሱ ፡ ብቻ ፡ እይደለም ።

አዲ ፡ ሊተኒ ።

ለኔም ፡ አዘነልኝ ፡ እንጅ ።

ወባሕቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሕሮ ።

ነገር ግን ፡ እግዚአብሔር እዘነለት ።

ከመ ፡ ትካዝ ፡ ዲበ ፡ ትካዝ ፡ ኢይትወሰኩኒ ፡ (ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፵፮ ፡ ኢሳ ፡ ፴፰ ፡ ፩ ።)

በኃዘን ፡ ላይ ፡ ኃዘን ፡ እንዳይጨመርብኝ ፡ (ሐተታ) ፡ በእስራት ፡ ላይ ፡ የደቀ ፡ መዝሙር ፡ ሞት ፡ በኃዘን ፡ ላይ ፡ ኃዘን ፡ ነውና ።

፳፰ ፡ ወፈነውክዎ ፡ ፍጡነ ፡ ከመ ፡ ትርአይዎ ፡ ወትትፌሥሑ ።

እይታችሁት ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ፈጥኜ ፡ ሰደድሁት ።

ወአነሂ ፡ ከመ ፡ እትፌሣሕ ፡(፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፲፰ ፡ ሮሜ ፡ ፲፮ ፡ ፪ ።)

እኔም ፡ የናንተን ፡ ነገር ፡ ሰምቼ ፡ ደስ ፡ ይለኝ ፡ ዘንድ ፡ ፈነውክዎ ። (ወተወከፍዎ ።) ማገናኛ ፡

፳፱ ፡ ወተወከፍዎ ፡ በእግዚእነ ፡ በኵሉ ፡ ፍሥሐ ።

ደስ ፡ ይለኝ ፡ ዘንድ ፡ ዘኪያክሙ ፡ ተወከፈ ፡ ኪያየ ፡ ተወከፈ ፡ ወዘኪያየ ተወከፈ ፡ ተወከፎ ፡ ለዘፈነ ወኒ ባለው ፡ በጌታችን ፡ ተወከፎ ፡ ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ ደስ እሰኝታችሁ ፡ ተቀበሉት ።

ወአክብርዎሙ ፡ ለእለ ፡ ከመዝ ።

እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ እነዚህንም ፡ አክብሯቸው (እለ) ፡ ዘመድ ፡ ዘመድ ፡ በሏቸው ፡ (ትቀበሏቸው ፡ ማለቱ ፡ ነው) ።

እስመ ፡ በእንተ ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽሐ ፡ እስከ ፡ ለሞት ።

የእግዚእብሔርን ፡ ሥራ ፡ ስለመሥራት ፡ እስከ ፡ መሞት ፡ ደርሷልና ።

ወመጠወ ፡ ነፍሶ ።

ሰውነቱንም ፡ ለመከራው ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷልና ፡ (እስከ ፡ መስጠት ፡ ደርሷልና) ፡ ሐተታ ፡ አስተዋፅ አውን ፡ ይዞ ፡ ሲሔድ ፡ እንደ ፡ ፎገራ ፡ ካለ ፡ ሜዳ ፡ ሲደርስ ፡ ንዳድ ፡ ታሞ ፡ ቀርቷል ።

ከመ ፡ ይፈጽም ፡ ዘአሕጸጽክሙ ፡ አንትሙ ፡ አመልእከተ ፡ ዚአየ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ፡ ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፳፬) ።

ከኔ ፡ ተልኮ ፡ ከናንተ ፡ የቀረውን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ (ሐተታ) ፡ አስተዋፅአውን ፡ ወስዶ] ፡ መስጠት ፡ ይገባቸው ፡ ነ ቦረ ፡ ንሱ ፡ ወስዶ ፡ ሰጥቶላቸዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ክ ፍ ል ፡ ፩ ።

፩ ፡ ወይእዜኒ ፡ እኁውየ ፡ ተፈሥሑ ፡ በእግዚእነ ።
እሁንም ፡ ወንድሞቼ ፡ በጌታችን ፡ በማመናችሁ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ።
ወዘሂ ፡ ዘእጽሕፍ ፡ ለክሙ ፡ ኢይትሐከይ ፡ እንስ ።
ይህንም ፡ ስጽፍላችሁ ፡ ነግ ፡ ሠልስት ፡ አላልኩም ።
እስመ ፡ ያጸንዓክሙ ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፲፭ ፡ ፩ ፡ ፩ ።)
እንዲያጸናችሁ ፡ አውቃለሁና ፡ (ወተዓቀቡ ፡ ማገኛ ።)
፪ ፡ ወተዐቀቡ ፡ እንትሙሂ ።
ነግ ፡ ሠልስት ፡ ሳልል ፡ የጻፍሁላችሁ ፡ እንዲያጸናችሁ ፡ አውቃለሁና ፡ (ተዐቀቡ ፡) ተጠበቁበት ፡ ብዬ ፡ ነው ።
ወዕቅዎሙ ፡ ለከለባት ። (ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፳፪ ፡ ፲፭ ፡ ኢሳ ፡ ፶፮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።)
በኒያ ፡ ለከፍካፎች ፡ ዕወቁባቸው ።
ወዕቅዎሙ ፡ ለገበርተ ፡ እኪት ።
በኒያ ፡ ክፉ ፡ አድራጎች ፡ ዕወቁባቸው ።
ወዕቅዎሙ ፡ ለምቱራን ፡ በግዝረት ።
በኒያ ፡ ግዙራን ፡ ነን ፡ በሚሉ ፡ ዕወቁባቸው ።
፫ ፡ ግዙራንስ ፡ ንሕነ ፡ እለ ፡ ንትለአክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመንፈስ ፡ (ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፳፱ ።)
ግዙራንስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በልቡና ፡ የምናገለግል ፡ እኛ ፡ ነን ።
ወናመልክ ።
የምናመልከው ።
ወንትሜካሕ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንመካለን ፡ እንጂ ።
፬ ፡ ወአኮ ፡ በሥጋነ ፡ ዘንትዌከል ።
በግዝረት ፡ የምንመካ ፡ አይደለም ።
እንዘ ፡ ብየ ፡ ግዝረት ።
እኔም ፡ ግዙር ፡ ስኾን ፡ ኢይትሜካሕ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ አልመካም ።
እመሰ ፡ አነ ፡ እትዌከል ፡ በግዝረት ።
በግዝረትስ ፡ መመካት ፡ የሚገባ ፡ ቢኾን ፡ እኔ ፡ ይልቅ ፡ እመካ ፡ ነበር ።
፭ ፡ ወእመሰበ ፡ ዘይሔሊ ፡ ትውክልተ ፡ በግዝረት ፡ (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፭ ፡ ፳፪ ።)
በግዝረት ፡ መመካት ፡ እንዲገባ ፡ የሚያስብ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ።
አነ ፡ እኄይስ ፡ ለዝንቱ ፡ ግዙር ፡ ዘበሳምንት ።
(እምዝንቱ ፡ ግዙር ፡ ዘበሳምንት ።) ዘኢተገዝረ ፡ ከተማ ፡ ነፍስቱ ፡ እመ ፡ ሳምንት ፡ ዕለት ፡ ባለው ፡ ከተ ገዝረ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ አይሁዳዊ ፡ እኔ ፡ እበልጣለሁ ።
(እኄይስ ፡ ለዝንቱ) ፡ ዘኢተገዝረ ፡ ከተማ ፡ ነፍስቱ ፡ እመ ፡ ሳምንት ፡ ዕለት ፡ ባለው ፡ የተገዘረ ፡ ቢጽ ሐሳዊ ፡ አይሁዳዊን ፡ እኔ ፡ እበልጠዋለሁ ፡ እንድም ፡ ሳምንትና ፡ የተገዘረ ፡ አረማዊን ፡ እኔ ፡ እበልጠ ዋለሁ ።
እኄይስ ፡ እምዝንቱ ።
ሳምንትና ፡ ከተገዘረ ፡ አረማዊ ፡ እኔ ፡ እበልጣለሁ ።
አንድም ፡ እንስ ፡ ግዙር ፡ በዘሳምንት ።
ዘኢተገዝረ ፡ ከተማ ፡ ነፍስቱ ፡ እመ ፡ ሳምንት ፡ ዕለት ፡ ባለው ፡ የተገዘርሁ ፡ እኔ ፡ (እኄይስ) ፡ ከቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ አይሁዳዊ ፡ እበልጣለሁ ። ሳምንትና ፡ የተገዘርሁ ፡ እኔ ፡ (እኄይስ) ፡ እበልጠዋለሁ ። ጌታ ፡ ባረገ በስምንት ዓመ[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

እምሕዝበ ፡ እስራኤል ።
ከእስራኤል ፤ ወገን ፡ የምኾን ።
እምነገደ ፡ ብንያም ።
ከዚያውም ፡ ከነገደ ፡ ብንያም ።
ዕብራዊ ፡ ዘእምዕብራውያን ።
ከዐዳውያን ፡ ፈለግ ፡ የምኾን ፡ ዐዳዊ ፡ ፈለግ ።
ወበሕገ ፡ ኦሪት ፡ ፈሪሳዊ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳፮ ፡ ፭ ።)
በሕገ ፡ ኦሪት ፡ ፈሪሳዊ ፡ የምኾን ። ፈሪሳዊ ፡ ማለት ፡ እሉል ፡ ባሕታዊ ፡ ማለት ፡ ነውና ።

፮ ፡ ወበቅንዓት ፡ ሰደድኩ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጽድቀ ፡ ኦሪት ፡ ንጹሐ ፡ ከዊንየ ።
ይህም ፡ ሊታወቅ ፡ በሃይማኖተ ፡ ኦሪት ፡ ጸንቼ ፡ ስለቀናሁ ፡ ምእመናንን ፡ ከዋሉበት ፡ አላሳድር ፡ ከአደሩበት ፡ አላውል ፡ እል ፡ ነበር ።

፯ ፤ ወባሕቱ ፡ ዝኩ ፡ ረባሕየ ፡ አብደርኩ ፡ እሕጕሎ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ። ማቴ ፡ ፲፫ ፤ ፵፬ ።
ዛሬ ፡ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ ስለአመንሁ ፡ በኦሪቱ ፡ እጠቀመዋለሁ ፡ ብየው ፡ የነበረውን ፡ ጥቅም ፡ ሳጣው ፡ ወደድሁ ።

፰ ፡ ወረሰይኩ ፡ ኵሎ ፡ ኀሣረ ፡ በእንተ ፡ ዕበየ ፡ ኃይለ ፡ አእምሮቱ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእየ ።
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የማወቅ ፡ ምሥጢር ፡ ስለበዛልኝ ፡ በኦሪት ፡ የነበርኩበትን ፡ ክብር ፡ እንደ ኃሣር ፡ አደረግሁ ።
እንድም ፡ በእንተ ፡ አእምሮተ ፡ ዕበየ ፡ ኃይሉ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
የክርስቶስ ፡ የኃይሉን ፡ ጽናት ፡ የክብሩን ፡ ብዛት ፡ ስላወቅሁ ፡ (ረሰይኩ ፡ ሐሠረ ፡) የነበርኩበትን ፡ ክብር ፡ ኹሉን ፡ እንደኢምንት ፡ አደረግሁት ።
ዘበእንቲአሁ ፡ ገደፍኩ ፡ ኵሎ ።
ስለርሱ ፡ ኹሉን ፡ የተውሁለት ።
ወረሰይክዎ ፡ ከመ ፡ ዕጸው ።
እንደጕድፍ ፡ ያደረግሁለት ።
ከመ ፡ እርብሖ ፡ ለክርስቶስ ፡ (ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፲፩) ።
ክርስቶስን ፡ ጥቅም ፡ እደርገው ፡ ዘንድ ።

፱ ፡ ወእኩን ፡ ቦቱ ።
በሱም ፡ በማመን ፡ ጸንቼ ፡ እኖር ፡ ዘንድ ።
እንዘ ፡ አልብየ ፡ ይእዜ ፡ ጽድቀ ፡ ኦሪት ፡ ዘእንበለ ፡ ጽድቀ ፡ ሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ (ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪።)
በሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ እንጂ ፡ በሃይማኖተ ፡ ኦሪት ፡ እከብራለሁ ፡ ማለት ፡ ሳይኖርብኝ ።
ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ።
(ክርስቶስ ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡) አካል ፡ ዘእምአካል ፡ ባሕርይ ፡ ዘእምባሕርይ ፡ የተወለደ ። እንድም ፡ ሃይማኖት ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ ግጠም ።

፲ ፡ ወቦቱ ፡ አእምሮ ፡ ለኢየሱስ ።
(ቦቱ ፡ ለጽድቀ ፡ ኦሪት ፡) በኦሪት ፡ ስለጸናሁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አውቄበታለሁና ፡ ምንም ፡ ባውቅበት ፡ በጽድቀ ፡ ኦሪት ፡ እከብራለሁ ፡ ማለት ፡ ሳይኖረኝ ። እንድም ፡ (ቦቱ ፡ በወንጌል ፡) በወንጌል ፡ ኢየሱስን ፡ አውቄበታለሁና ፡ ገደፍኩ ፡ ኵሎ ።
ወበኃይለ ፡ ትንሣኤቱ ፡ (ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፫-፭ ።)
የትንሣኤውንም ፡ ምስጢር ፡ አውቄበታለሁ ።
ወእሳተፍ ፡ በሕማሙ ፡ ወእትሜሰሎ ፡ በሞቱ ፡ (ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፯ ፡ ገላ ፡ ፮ ፡ ፲፯ ።)
ስለዚህ ፡ በመከራውም ፡ እተባበረዋለሁ ፡ በሞቱም ፡ እመስለዋለሁ ፡

፲፩ ፡ እመቦ ፡ ከመ ፡ እድምዮ ፡ በዝንቱ ፡ እመ ፡ ይትነሥኡ ፡ ምውታን ።
ሙታን ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ እገኘው ፡ እንደኾነ ፡ ብዬ ፡ የማገኘው ፡ ማግኘት ፡ እንዳለ ፡ ብዬ ።
ወእኮሰ ፡ ዘወዳእኩ ፡ ወነሣእኩ ፡ ወሠለጥኩ ፡ ዘንተ ።
ነገር ፡ ግን ፡ መከራውን ፡ ፈጽሜ ፡ የተቀበልሁ ፡ እይደለም ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪ ፡ ዳዕሙ ፡ እዴግን ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ።)
ገና ፡ እከታተላለሁ ፡ እንጂ ።
ለእመ ፡ እረክብ ፡ ግብረ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ነሥአኒ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፱ ፡ ፮ ። )
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እኔን ፡ የሾመበትን ፡ ግብር ፡ እፈጽም ፡ እንደኾነ ፡ ብዬ ። እንድም ፡ እኔን ፡ የመ
ረጠለትን ፡ ክብር ፡ አገኝ ፡ እንደኾነ ፡ ብዬ ።

፲፫ ፡ አ ፡ አኃውየ ፡ ሊተሰ ፡ ይመስለኒ ፡ ዓዲየ ፡ ኢነሣእኩ ፡ ፍጻሜ ፡ (ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፳፮ ።)
እኔስ ፡ ወንድሞቼ ፡ ገና ፡ ከፍጹምነት ፡ ያልደረስሁ ፡ ይመስለኛል ። የደረስሁ ፡ አይመስለኝም ።
እስመ ፡ ዘድኅሬየ ፡ እረስዕ ፡ ወዘቅድሜየ ፡ እሜልዕ ፡ ወእዴግን ።
የኋላዬን ፡ እዘነጋዋለሁ ፡ የፊቴን ፡ እከታተላለሁና ፡ (ሐተታ ፡ ) ከመንገደኛ ፡ አብነት ፡ ነሥቶ ፡ ተና
ገረ ፡ መንገደኛ ፡ ሲሔድ ፡ ውሎ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ቀረኝ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ያለፈውን ፡ እንዳያስብ ።

፲፬ ፡ ወእኃሥሥ ፡ ዕሤትየ ፡ ከመ ፡ ሰብአ ፡ ዓይን ፡ ለጽዋዔ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ላዕሉ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፳፬ ፡ ቈላስ ፡ ፫ ፡ ፪ ።
በእግዚአብሔር ፡ ጠሪነት ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቃል ፡ ወደሰማያዊ ፡ አጠራር ፡ ለመጠራት ፡ እንደ
ጉበኛ ፡ ዋጋዬን ፡ እሻለሁ ፡ (ሐተታ ፡) ጉበኛ ፡ ጌሸኛ ፡ አሥነሥቶ ፡ አንባ ፡ እሰብሮ ፡ ሀገር ፡ እስወርሮ ፡
በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ዋጋውን ፡ እንዲሻ ። እንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ህልውና ፡ በኔ ፡
አድሮ ፡ ምእመናንን ፡ ለጠራላት ፡ ለሰማያዊት ፡ አጠራር ፡ ጉበኛ ፡ እንደመኾኔ ፡ ዋጋዬን ፡ እሻለሁ ።

፲፭ ፡ ኵልክሙ ፡ ፍጹማን ፡ ዘንተ ፡ ሐልዩ ።
በልደተ ፡ ነፍስ ፡ ፍጹማን ፡ የምትኾኑ ፡ ኹላችሁም ፡ ይህን ፡ አስቡ ፡ አንድም ፡ ሕዝቡ ፡ ሳይበቁ ፡
ዲቁና ፡ ዲያቆናቱ ፡ ሳይበቁ ፡ ቅስና ፡ ተመኝተዋልና ፡ በፍና ፡ ተሣልቆ ፡ ኵልክሙ ፡ ፍጹማን ፡ አለ ።
ወእመኒቦ ፡ ባዕድ ፡ ዘትሔልዩ ፡ ኪያሁኒ ፡ ይከሥት ፡ ለክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ዕብ ፡ ፮ ፡ ፲፬ ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡
፲፩ ፡ ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፲ ፡ ፯ ።)
ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ያሰባችሁት ፡ ቢኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዚያ ፡ ያብቃችሁ ።

፲፮ ፡ ወባሕቱ ፡ ውስተ ፡ ዘበጽሕነ ፡ ግብር ፡ ናጥብዕ ፡ በአሐዱ ፡ ኀብረት ፡ (ገላት ፡ ፮ ፡ ፲፮ ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፰ ።)
ነገር ፡ ግን ፡ እስከዚያ ፡ ባለንበት ፡ ግብር ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾነን ፡ እንጽና ።

፲፯ ፡ ኪያየ ፡ ተመሰሉ ፡ አኃውየ ።
ወንድሞቼ ፡ እኔን ፡ ምሰሉ ።
ወተዓቀብዎሙ ፡ ለእለ ፡ ከመዝ ፡ የሐውሩ ።
እንዲህ ፡ ባለ ፡ አነዋር ፡ በሚኖሩ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ሰወቁባቸው ።
ዘከመ ፡ ትሬእዩኒ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፩ ።)
እኔን ፡ እንደምታዩኝ ።

፲፰ ፡ እስመ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ ሖረተ ፡ ካልአ ።
ከኛ ፡ ልዩ ፡ በኾነ ፡ አነዋር ፡ የሚኖሩ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ።
ዘከመ እብለክሙ ፡ ዘልፈ ።
አስቀድሜ ፡ እንደነገርኋችሁ ።
ወይእዜኒ ፡ ገሃደ ፡ እነግረክሙ ።
ዛሬም ፡ ገልጬ ። እነግራችኋለሁ ።
ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ጸላዕቱ ፡ ለመስቀለ ፡ ክርስቶስ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ፡ ገላት ፡ ፮ ፡ ፲፪ ።
የክርስቶስ ፡ መከራ ፡ መስቀል ፡ ጠላቶች ፡ እንደኾኑ ።

፲፱ ፡ እለ ፡ ደኃሪቶሙ ፡ ለሕርትምና ።
ፍጻሜያቸው ፡ ለጥፋት ፡ እንደኾነ ።
እለ ፡ ከርሦሙ ፡ ያመልኩ ።
ሆድ ፡ አምላኩ ፡ እንደኾኑ ።
ወክብሮሙ ፡ ኃሣሮሙ ።
ክብረ ፡ ሥጋቸው ፡ ኃሣረ ፡ ነፍስ ፡ የሚኾንባቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

እለ ፡ ይሔልዩ ፡ ዘውስተ ፡ ምድር ። (ሮሜ፡ ፲፮፡ ፲፰ ።)
(ይሄልዉ ።) በምድራዊ ፡ ግብር ፡ የሚኖሩ ።
(ይሔልዉ ።) ምድራዊ ፡ ነገርን ፡ የሚሹ ።

፳ ፡ ወለነሰ ፡ ዘውስተ ፡ ሰማያት ፡ ሀገርነ ፡ (ኢፌ፡ ፪፡ ፯ ፡ ቈላስ፡ ፫፡ ፩፡ ዕብ፡ ፲፪፡ ፳፪፡ ቲቶ፡ ፪፡ ፲፫ ።)
የኛስ ፡ አነዋወራችን ፡ በሰማያዊ ፡ ግብር ፡ ነው ። አንድም ፡ የምንሻው ፡ ሰማያዊ ፡ ግብርን ነው ።
ወእምህየ ፡ ንጸንሕ ፡ ኪያሁ ፡ መድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ።
በሰማያዊ ፡ ግብር ፡ ኾነን ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ደጅ ፡ እንጠናሰን ።

፳፩ ፡ ዘይሔድስ ፡ ሥጋነ ፡ ትሑተ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፵፫ ፡ ፶፱ ፡ ፶፫ ።)
ግዙፉ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ብሉይ ፡ ሥጋችነን ፡ የሚያድሰው ።
ወይሬስዮ ፡ አምሳለ ፡ ሥጋ ፡ ስብሐቲሁ ።
የጌትነት ፡ ክብር ፡ የተፈጸመበት ፡ ሥጋውን ፡ የሚያስመስለው ።
እንድም ፡ የጌትነት ፡ ክብር ፡ እንደተፈጸመበት ፡ እንደሥጋው ፡ የሚያደርገው ።
በከመ ፡ ረድኤተ ፡ ኃይሉ ።
እንደ ፡ ከሐሊነቱ ፡ አጋዥነት ፡ መጠን ፡ ንጸንሕ ኪያሁ ።
ዘቦቱ ፡ ይገኒ ፡ ሎቱ ፡ ኵሉ ።
ኹሉ ፡ የሚገዛለት ፡ ብሉ ፡ ኃይል ፡ ላለው ፡ ቀጸል ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ክፍል ፡ ፳ ።

፩ ፡ ወይእዜኒ ። አኃዊነ ፡ ፍቁራን ፡ ፍሥሓነ ፡ ወእክሊልነ ።
አሁንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትወዱ ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚወዳችሁ ፤
እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ የምትዋደዱ ፡ ወንድሞቻችን ፤ ደስታችን ፡ ክብራችን ፡ ናችሁ ።
ከመዝ ፡ ቁሙ ፡ ወጽንዑ ፡ በእግዚእነ ፡ አኃዊነ ። (፪፡ ቆሮ፡ ፩፡ ፲፬ ። ፩፡ ተሰሎ፡ ፪፡ ፲፱፡ ፳ ።)
(እመ ፡ ትቀውሙ ) ፡ እንዲህ ፡ በጌታችን ፡ በማመን ፡ ብትጸኑ ፡ ደስታችን ፡ ክብራችን ፡ ናችሁ ። አን
ድም ፡ ፍቁራን ፡ ፍሥሐን ።
ደስታችነን ፡ ክብራችነን ፡ የምትወዱ ፡ ወንድሞቻችን ፡ (ከመዝ ፡ ቁሙ ፡ ወጽንዑ)፡ እንዲህ ፡ በጌ
ታችን ፡ በማመን ፡ ጽኑ ።
፪ ፡ ወእስተበቍዓክሙ ፡ ኢዎድያን ፡ ወስንጣክን ፡ ከመ ፡ ተሐልዩ ፡ በቶልእኮ ፡ እግዚእነ ፡ በአሐዱ ፡ ልብ ።
(ም ፡ ፪ ፡ ፪ ። )
ኢውድያን ፤ ስንጣክን ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾናችሁ ፡ ጌታችንን ፡ የምታገለግሉበትን ፡ ግብር ፡ ትይዙ ፡
ዘንድ ፡ እማልዳችኋለሁ ።
፫ ፡ ወእስተበቍአከ ፡ ለከሂ ፡ እኁየ ፡ ወመጻምርትየ ፡ ሰትረካ ፡ ከመ ፡ ታርድአሙ ።
አንተም ፡ ወዳጄ ፡ እጥላቆቴ ፡ ሰትረካ ፡ ትረዳቸው ፡ ዘንድ ፡ እማልድሃለሁ ።
እስመ ፡ ሠርሑ ፡ ምስሌየ ፡ በትምህርተ ፡ ወንጌል ።
ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ እንደኔ ፡ ደከመዋልና ።
ምስለ ፡ ቀሌምንጦስ ።
(ሠርሑ ፡ ምስለ ፡ ቀሌምንጦስ ) ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ ከቀሌምንጦስ ፡ ጋራ ፡ ደክመዋልና ።
( ታርድአሙ ፡ ምስለ ፡ ቀሌምንጦስ ) ፡ ከቀሌምንጦስ ፡ ጋራ ፡ ትረዳቸው ፡ ዘንድ ።
ወኵሎሙ ፡ ቢጽነ ፡ እለ ፡ አሐዱ ፡ ግብሮሙ ።
በሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ከሚኾኑ ፡ ከወንድሞቻችን ፡ ጋራ ፡ ትራዳቸው ፡ ዘንድ ።
እለ ፡ ተጽሕፈ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡ (ፊል፡ ፪፡ ራእ፡ ፲፫፡ ፳፡ ሉቃ፡ ፲፡ ፳ ።
ስማቸው ፡ በልዑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለበጎ ፡ የታወቀ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፡ ፬ ።

፬ ፡ ተፈሥሑ ፡ በእግዚእነ ፡ ዘልፈ ።
ኹልጊዜ ፡ በጌታችን ፡ በተደረገላችሁ ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ።
ወካዕበ ፡ እብለክሙ ፡ ተፈሥሑ ፡ (ም፡ ፫፡ ፩፡ ፪፡ ቆሮ፡ ፲፫ ፤ ፲፩ ። ኢሳ፡ ፷፩፡ ፲ ።)
እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ በሚደረግላችሁ ፡ ነገር ፡ ዳግመኛ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፤ ይላቿኋል
፭ ፡ ወይትዐወቅ ፡ ሥላጤክሙ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ (ቲቶ፡ ፫፡ ፪፡ ያዕ፡ ፩፡ ፰፡ ፱ ።)
ፍጹምነታችሁ ፡ በሰው ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ሊታወቅ ። (በሕዝቡም ፡ በአሕዛብም) ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው።
እግዚአብሔር ፡ ቅሩብ ። (፩፡ ቆሮ፡ ፲፡ ፲፩ ፡ መዝ፡ ፴፬፡ ፲፰ ። መዝ፡ ፻፵፭ ፡ ፲፰ ።)
አይለያችሁምና ።
፮ ፡ ኢተሐልዩ ፡ ወኢምንተኒ ። (ማቴ፡ ፮፡ ፳፭፡ ፩፡ ጴጥ፡ ፭፡ ፯ ።)
በምንም ፡ በምን ፡ አታስቡ ።
ወባሕቱ ፡ ጸልዩ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወ ሰአሉ ። (መዝ ፡ ፻፵፩ ፡ ፲፰ ።)
ነገር ፡ ግን ፡ በየጊዜያቱ ፡ ኹሉ ፡ ጸልዩ ፡ ለምኑ ።
ወእንዘ ፡ ተአኵቱ ፡ ክሥቱ ፡ ስእለተክሙ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ። (መዝ ፡ ፴፯ ፡ ፭ ።)
ስትለምኑም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ገልጣችሁ ፡ ንገሩት ።
፯ ወሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንተ ፡ ኵሉ ፡ ባቲ ። (ዮሐ፡ ፲፬፡ ፳፯፡ ቈላስ፡ ፫፡ ፲፭፡ ሮሜ፡ ፭፡ ፯ ።)
ኹሉ ፡ የሚደረግባት ።
ወትትሌዓል ፡ እምኵሉ ፡ ልብ ።
ከልብ ፡ ኹሉ ፡ የምትርቅ ፡ ( እለ ) ፡ ልቡና ፡ መርምሮ ፡ የማይደርስባት ።
ወእምኵሉ ፡ ሕሊና ፡ ታጽንዖ ፡ ለልብክሙ ፡ ወለሕሊናክሙ ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ።
ከሕሊና ፡ ኹሉ ፡ የምትርቅ ፡ ( እለ ) ፡ ሕሊና ፡ መርምሮ ፡ የማይደርስባት ፡ ተዋሕዶ ። (አንድም ፡) መን
ፈስ ። ቅዱስ ፡ ልቡናችሁን ፡ ሕሊናችሁን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማመን ፡ ታጽናው ።
፰ ፡ ወይእዜኒ ፡ እኀዊነ ፡ ኵሉ ፡ ዘርትዕ ። (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፲፯ ፡)
አሁንም ፡ ወንድሞቻችን ፡ የጠማምነቱን ፡ ትታችሁ ፡ የቅንነቱን ።
ወዘንጽሕ ።
የኃጢአቱን ፡ ትታችሁ ፡ የንጽሕናውን ።
ወዘጽድቅ ።
የሐሰቱን ፡ ትታችሁ ፡ የውነቱን ።
ወዘሠናይ ።
የክፉውን ፡ ትታችሁ ፡ የበጎውን ።
ወዘፍቅር ።
የጠቡን ፡ ትታችሁ ፡ የፍቅሩን ።
ወዘምድኅር ።
የመራገሙን ፡ ትታችሁ ፡ የመመረቁን ።
ወእስተርክቦ ዘይደሉ ።
ልቡና ፡ የማባከኑን ፡ ትታችሁ ፡ የመሰብሰቡን ።
ዘይደሉ ፡ ብሎ ለእስተርክቦ ፡ ቀጠለ ፡ እንድም ፡ ለኹሉም ፡ ቀጠለ ፡ አንድም ፡ ወዘይደሉ ፡ ይላል ፡ የማይገባውን
ትታችሁ ፡ የሚገባውን ።
ወዘይትአኰት ።
የማይመሰገነውን ፡ ትታችሁ ፡ የሚመሰገነውን ።
ኪያሁ ፡ ሐልዩ ።
እሱን ፡ ያዙ ።
፱ ፡ ዘተመሀርክሙ ፡ ወዘሰማዕክሙ ፡ ወዘርኢክሙ ፡ በኀቤየ ፡ ኪያሁ ፡ ግበሩ ።
ከኔ የተማራችሁትን ፡ ከኔ ፡ የሰማችሁትን ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ ያያችሁትን ። ያንን ፡ ሥሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወአምላከ ፡ ሰላም ፡ የሀሉ ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ። (፩፡ ተሰሎ ፡ ፭ ፡ ፳፫ ፡)
የፍቅር ፡ የአንድነት ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ አድሮባችሁ ፡ ይኑር ።
ይደርባችሁም ፡ ቢል ፡ ይኾናል ።

፲ ፡ ተፈሣሕኩ ፡ በእግዚእነ ፡ ፈድፋደ ።
በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተደረገልኝ ፡ ነገር ፡ በማመን ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ አለኝ ።
እስመ ፡ ትሔልዩ ፡ ወትጽሕቁ ፡ ለትካዝየ ፡ እምቀዲሙ ። (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፱ ፡)
ከጥንተ ፡ ስብከት ፡ ጀምሮ ፡ ግዳጄን ፡ ለመፈጸም ፡ ትሻላችሁና ።
በከመ ፡ ትጽህቁ ፡ ሊተ ፡ ዓዲ ።
ከዚህን ፡ ቀደም ፡ ብቻ ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ እንድትሹ ፡ አውቃለሁ ።
ወለእመ ፡ ይሰዐነክሙ ።
ምንም ፡ ቢሳናችሁ ። አንድም ፡ ቢሳናችሁም ፡ ኢትተክዙ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ አትዘኑ ።

፲፩ ፡ ወአኮ ፡ ዘእቤ ፡ በእንተ ፡ ዘኃጣእኩ ።
እንዲህም ፡ የምል ፡ ስለቸገረኝ ፡ አይደለም ።
እስመ ፡ አእምር ፡ ከመ ፡ የአክለኒ ፡ ዘብየ ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፮ ፡)
ያለኝ ፡ እንዲበቃኝ ፡ አውቃለሁና ፡ ። ( ሐተታ ፡ ) ምን ፡ አለው ፡ ቢሉ ፡ የዕለት ፡ እራት ፤ ተግባር ፤ ሃይማኖት ።

፲፪ ፡ ከሀሊ አንሰ ፡ (፪፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲ ) (እኔ ፡ እችላለሁ ።)
ተጽናስሂ ። ችግሩንም ።
ወተፈሥሖሂ ።
ተድላ ፡ ደስታውንም ፡ ( ሐተታ ፡ ) ቅዱሳን ፡ አንዳንድ ፡ ቀን ፡ ለሰው ፡ ብለው ፡ የሚያደርጉት ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አለና ።
በኵሉ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ለመድኩ ።
ኹሉን ፡ በኹሉ ፡ ለምጃለሁ ።
ርኂበሂ ። (፪ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፯ ፡)
መራቡንም ፤ ( ተጽናስሂ ፡ ላለው ) ።
ወጸጊበሂ ።
ጥጋቡንም ፤ ( ተደልዎሂ ላለው ) ።
ሐሚመሂ ።
ኃዘኑንም ፤ ( ርኂበሂ ፡ ላለው ) ።
ወተፈሥሖሂ ።
ተድላ ፡ ደስታውንም ፤ ( ጸጊበሂ ፡ ላለው ) ።

፲፫ ፡ ኵሎ ፡ እክል ፡ በዘወእቱ ፡ አክሀለኒ ፡ ክርስቶስ ፡ (፪፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፲ ፡ ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፳፱ - ፴፩ ።)
( ውእቱ ፡ ክርስቶስ ) ፡ እሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ባስቻለኝ ፡ ገንዘብ ፡ ኹሉን ፡ እችላለሁ ፡

፲፬ ፡ ወባሕቱ ፡ ሠናየ ፡ ገበርክሙ ፡ ዘተሳተፍክሙ ፡ በሕማምየ ።
ነገር ፡ ግን በመከራዩ ፡ የመሰላችሁኝ ፡ በጎ ፡ አደረጋችሁ ።

፲፭ ፡ ተአምሩ ፡ አንትሙ ፡ ሰብአ ፡ ፊልጵስዩስ ፡ በቀዳሚ ፡ ትምህርት ፡ አመ ፡ መጻእኩ ፡ እመቄዶንያ ፡ ከመ ኢኅብሩ ፡ ምስሌየ ፡ አሐዱሂ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፱ ።)
እናንተ ፡ የፊልጵስዩስ ፡ ሰዎች ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ከመቄዶንያ ፡ ወደናንተ ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ከምእመናን ፡ እንዱስ ፡ እንኳን ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንዳልኾነ ፡ ታውቃላችሁ ።
ኢበውሂብ ። እሱ ፡ በመስጠት ።
ወኢበነሢእ ።
እኔ ፡ በመቀበል ፡ አንድ ፡ እንዳልኾነ ፡ ታውቃላችሁ ።
ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ባሕቲትክሙ ።
ከናንተ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ እናንተ ፡ ብቻ ፡ ናችሁ ፡ እንጂ ።

www.ethiopianorthodox.org